# <u>የሰላም ንድፈ ሓሳቡ ላይ ያለን እይታ!</u>

በሰሜን አሜሪካ የኢሮብ ኮሚኒቲ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ኅዳር 16 ቀን 1997 ዓ.ም በኢትዮ ኤርትራ ውዝግብ አፈታት ላይ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረቡትን ባለ 9 ገጽ አዲስ የሰላም ሓሳብን በከፍተኛ ጥንቃቄ ተመልክቶታል ። በተጨማሪም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተሩና የማስታወቀያ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ በረኸት ስምዖን የሰጡዋቸው የተለያዩ የፕረስ ውጤቶችንም ሲከታተል ቆይቷል ። እነዚህን በሙሉ መርምሮ ሲያበቃም አጠቃላይ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በሚዛን አስቀምጦ ገምግሟል ። በዚህ ግምገማ መሠረት ኮሚኒቲው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀርቦ በተወካዮች ምክርቤት የጸደቀው ”የሰላም” ሓሳብ ከሚያመጣው መልካም ውጤት ይልቅ የሚያስከትለው ሰብአዊና ማተሪያላዊ ጥፋት እጅጉን የላቀና አስከፊ ሊሆን እንደሚችል በሚገባ ተገንዝቧል ። ከዚህም በተጨማሪ የኢሮብ ህዝብ በኢትዮጵያ ፓርላማ ውስጥ የራሱ ተወካይ የነበረው ቢሆንም ፡ ወኪሉ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ በህዋላ ተተኪ ወኪል መርጦ እንዲልክ በምርጫ ቦርድም ሆነ በምክር ቤቱ አፈጉባኤ የተደረገ ጥረት የለም ። በመሆኑም ዛሬ በህልውናው ላይ እየተፈረደበት የሚገኘው የኢሮብ ህዝብ የገጠመው ከፍተኛ ችግር በራሱ ጉዳይ ላይ እንደ ህዝብ ራሱ እንዲወስንና በጉዳዩ ላይ እንዲመክር ዕድሉን መነፈጉ ብቻ ሳይሆን በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የነበረው የውክልና ቦትንም በመነፈጉ በምክር ቤቱ ውስጥ የተቃውሞ ድምጹን ለማሰማት የምችልበት መሠረትም ተነፍጎት ይገኛል ። ይህ አሠራር የኢሮብ ህዝብን እንደሚጎዳ እንኳን የኢትዮጵያ የፓርላማ አባል ሌላ ማንም ጉዳዩን የተከታተለ ሰው የሚገነዘበው ሲሆን ፡ የሚያስከትለው ቀውስም አሁን እንደሚታየው ባንድ የተወሰነ አከባቢ ተወስኖ የሚቀር እንደማይሆንም ተመልክቷል ። ችግሩ አጠቃላይ ቀጠናውን ሊነካ የሚችል ፡ የየራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ሲሉ የተለያዩ ኃይሎች አንዱን በመወገን ሌላውን ለማዳከም በተለያየ መልክ እጃቸውን ለማስገባት የሚችሉበት ዕድልን የሚያሰፋ የፉክክር ቀጠና ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ወስዷል ። ባጠቃላይ ውጤቱም የመጀመርያው የጉዳቱ ገፈት ቀማሽ በነዚህ ” አወዛጋቢ” እየተባሉ በሚጠሩ ፡ በበኩላችን ግን ምንም የሚያወዛግብ ችግር የማናይባቸው አከባቢዎች ነዋሪ ሕብረተሰብ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ፡ በረጅሙ ሲታይ መላውን የአፍሪቃን ቀንድ ሊያተራምስ የሚችል ቀውስ እንደሚያስከትል ግንዛቤ ወስደናል ።

ለዚህ ግንዛቤአችን መነሻ የሆነን ከላይ እንደተገለጸው አቶ መለስ የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ውዝግብን ለመፍታት ያቀረቡትና ከ10 የተቃዋሚ ፓርቲዎች የፓርላማ አባላት በስተቀር በገዥው ፓርቲ አባላት ሙሉ በሙሉ ተደግፎ የጸደቀው ባለ 5 ነጥብ ”የሰላም” ሓሳብ ነው ።

<u>በመጀመሪያ ደረጃ</u> ችግሮች በሰላም መፈታት አለባቸው የሚለው መሠረተ ሓሳብ በጽንሰ ሓሳብ ደረጃ እጅጉን የምንደግፈውና መሆንም የነበረበትና ያለበት መሆኑን እንደምናምን በግልጽ ለማስቀመጥ እንወዳለን ። ይህንን የምናምነውም ”ይህንን የሰላም ሓሳብ ያልደገፈ ፀረ ህዝብ ነው” እንዳንባል ብለን ሳይሆን በመርህና በእምነት ለሰላም ያለን ፍላጎትና ጉጉት እጅጉን የላቀ በመሆኑ ነው ። ሰላም በማጣታችን ምክንያት እስከዛሬ ስማቸውን አንስቶ የደረሱበትን እንኳ ለማወቅ በመንግሥት በኩል ምንም ጥረት ሳይደረግ እንዲሁ ሻዓቢያ እንደወሰዳቸው ጠፍተው የቀሩ ጠያቂ አልባ ዘመድ ወገኖቻችን እንዳሉ በግልጽ የሚታወቅ በመሆኑ ነው ። ሰላም ቢኖር ቢያንስ እነዚህን የምናፈቅራቸው ወንድም እህቶቻችን ዛሬ በመካከላችን ሊገኙ ይችሉ እንደነበር እናምናልን ። ሰላምን የምንፈልገውም ከዚ አንጻር ነው ። ስለዚህም ችግራችን ሰላማዊ መፍትሔ መሻቱ ላይ እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽ እንዲሆን እንፈልጋለን ።

ችግራችን የምንፈልገው ሰላም ምን ዓይነት ሰላም ነው ? የሚለው ላይ ነው ።

ከላይ የተጠቀሰው ሰነድ ውስጥ ገጽ 2 ላይ ባለው የመጀመርያ ፓራግራፍ ውስጥ ". . የኤርትራ ህዝብ ነፃ መንግሥት ማቋቋም ፍላጎቱ እንደሆነ ባረጋገጠበት ወቅት ኢትዮጵያ ይህንኑ የህዝብ ውሳኔ በፀጋ ተቀብላ ለኤርትራ ነፃነት እውቅና የሰጠች የመጀመርያዋ አገር ሆናለች ።" ይላል ። ችግሩ አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት የህዝቦች ፍላጎትን ለማክበር የተቸገረው ለምንድነው የሚለውን ጥያቄ አንስተን ተገቢ መልስ ለማግኘት አለመቻላችን ላይ ነው ያለው ። ከዚህም አልፎ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የፓርላማ አባላት በዕለቱ በጉዳዩ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲመክርበትና እንዲወያይበት ሲያሳስቡ የቀረበው የሰላም ሓሳብ ላይ ህዝባዊ ውይይት እንደማይካሄድ በግልጽ ቋንቋ ሲነገራቸው ተደምጧል ። ለምን ? የኤርትራ ህዝብ ፍላጎቱን እንዲገልጽ በመፍቀድ ውሳኔውን በፀጋ የተቀበለ መንግሥታችን የገዛ ህዝቡን በራሱ ጉዳይ ላይ ለማወያየት የሚፈራበት ምክንያት ለኛ የችግሩ ሰለባ ለሆን ዜጎች ሊገባን የሚችል ጉዳይ አይደለም ። የመንግሥታችን መሠረታዊ አቋም የህዝቦች ፍላጎትና ውሳኔ "በፀጋ" መቀበል እስከሆነ ድረስ ፡ በዚህ መሠረታዊ አቋም የኤርትራ ህዝብ ተጠቃሚ የሆነውን ያህል የአሮብ ህዝብና የሌሎችም ያለ አገባብ ለኤርትራ በተከለሉ አከባቢዎች ነዋሪ ኢትዮጵያዊያን ተጠቃሚ መሆን ይኖርባቸዋል ። መንግሥታችን በዚህ አቋም ላይ ሁለት መመዘኛዎች ይዞ ሊቀርብ የሚሞክርበት መሠረታዊ ጉዳይ ሊኖሮው አይችልም ። ቢኖርም እንኳ ይህ ጉዳይ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊያን  የበለጠ የሚጠቅም መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለምንመኘው ዘላቂ ሰላም መምጣት መተክያ የሌለው ዋናው ቁልፍ ያለው በህዝቡ እጅ በመሆኑ ከዚህ የመንግሥት አቋም ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ መሆን አለበት እንላልን ።

<u>በሁለተኛ ደረጃ</u> ፤ እንደዚሁ ገፅ 2 ላይ "ይሁንና በሂደት በሁለቱ አገሮች መካከል የሚኖረው የኢኮኖሚ ግንኙነት በጋራ ጥቅም ላይ እንዲመሠረት በማድረግ ረገድ በኤርትራ መንግሥት በኩል ተገቢ ያልሆነ አቋም በመያዙ አለመግባባቶች እየተፈጠሩና እየተባባሱ መሄድ ጀመሩ ።....... ይልቁንም ችግሮቹ እየተወሳሰቡ ሂደው በመጨረሻ የኤርትራ መንግሥት ግንቦት 1990 ዓ.ም ላይ ግልጽ ወረራ የሰነዘረበት ደረጃ ላይ ደረሰ ።" ይላል ።

እዚህ ውስጥ የተፋለሱ ነገሮች መኖራቸው በግልጽ ይታያል ። ቢያንስ ለኛ እንደሚገባን ከሆነ የጦርነቱ መሠረታዊ መነሻ ባድመ ወይም የአሮብና ጉለመኻዳ የድንበር ጥያቄ ሳይሆን የኢኮኖሚ ግንኙነት መሆኑ ግልጽ ሆነዋል ። ለሰላም የቀረቡት 5 ነጥቦች ውስጥ ግን ምናልባት በተራ ቁጥር 2 ላይ የሰፈረው ይበልጥ ሲብራራ የኢኮኖሚ ግንኙነቱን ይገልጽ እንደሆን እንጂ አሁን በሚታየው መልኩ ስንመለከተው 5ቱም ነጥቦች የሚዘረዝሩት ስለ ድንበር መካለል ሆነው እናገኛቸዋለን ። እዚህ ላይ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ማንሳት የግድ ይላል ።

ሀ/ የጦርነቱ መነሻ የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው ከተባለ የኢኮኖሚ ገንኙነቱን ያሻከሩ ለዩነቶች እስካልተፈቱ ሉዓላዊነታችንን አስደፍረን ፡ የዜጎቻችንን የኢትዮጵያዊነት መብት አስገፍፈን ፡ ይህ ነው የማይባል የተከፈለው መስዋዕትነት ውኃ በልቶት ሰላም እንፍጠር ቢባል ፡ መሠረታዊ የሻዓቢያ ጥያቄ አሁንም ስላልተስተናገደ ሻዓቢያን መሬታችን ስለሰጠነው ጦርነት ከመጫር የሚቆጠብ ለመሆኑ ምን ዋስትና አለን ? መንግሥታችን ለዚህ የሚሰጠን ዋስትና ምንድ ነው ? መቼም መሬት ከወሰደ ተመልሶ አይነካንም የሚል አይሆንም ! ወይም ያኔ ዓለም ያውቅልናል ፡ "ወዳጆቻችን" ይኮንኑታል የሚል ሊሆንም አይችልም ! ያኔ እንዳዲስ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንሆናለንም ኪሳራችን ብዙ ነውና የሚያዋጣን አይሆንም ! መልሱን ከመንግሥታችንና ከፓርላማ ተወካዮቻችን አሁኑኑ በግልጽ ሊነገረን ይገባል እንላለን ።

ለ/ መሠረታዊ የጦርነቱ መነሻ ድንበር ካልሆነ የአልጀርሱ ስምምነት ውስጥ የኢኮኖሚ ግንኙነትን በሚመለከት መንግሥታችን የተወሰኑ አንቀጾች እንዲጨመሩ ለምን አልተንቀሳቀሰም ? (ለነገሩ የመንግሥትና የአዲሱ የሰላም ዕቅድ በመሆኑ አነሳነው እንጂ የሔጉን ፍርደ ገምድል ውሳኔ መነሻ የአልጀርስ ስምምነት መሆኑ ስላጣነው እንዳልሆነ ግንዛቤ እንዲያገኝልን እንፈልጋለን ።) የችግሩ መነሻ የኢኮኖሚ ግንኙነት መሆኑ እየታወቀ ችግሩ ከሥሩ ካልተፈታ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ እንደማይችል በወቅቱ ለመገንዘብ እንዴት ሳይችል ቀረ የሚሉ ጥያቄዎች ቅንና ቀጥተኛ መልስ ካላገኙ የምንመኘው ዘላቂ ሰላም ሊመጣ እንደማይችል አሁንም ቢሆን ግንዛቤ እንዲያገኝ ጥሪ እናቀርባለን ።

<u>በሶስተኛ ደረጃ</u> ፤ ገጽ 3 ላይ "ውሳኔው ከሕግ ውጭና ኢፍትሐዊ የነበረ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን ሕገ ወጥና ኢፍትሐዊ ውሳኔ እንደሚቃወም በወቅቱ ገልጿል ።" ይልና ወረድ ብሎ ደግሞ ". . . . ለላቀ አላማና ጥቅም ሲባል ኢፍትሐዊ ውሳኔዎችን እየተቃወሙም ቢሆን መተግበር እንደሚቻልና ይህንን ማድረግ ተገቢ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ይገነዘባል ።" ይላል ። እዚህ ውስጥም ግድፈት ይታየናል ። በመጀመርያ ላይ እንደተደረገው ኢፍትሓዊ ውሳኔን አለመቀበል በመርህ ደረጃም ሆነ በስትራተጂ አገባብነት አለው ። የተካሔደብን ወረራን ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ዳር ድንበራችንን ማስከበራችን ሕጋዊም ፍትሓዊም እንደነበረና እንደሆነም ከልብ እናምናለን ። ወረራውን በመስዋዕትነት ለመቀልበስ የተወሰደው እርምጃም መሠረታዊ ዓላማው ዳር ድንበራችንን ለማስከበር እንጂ ሌላ ዓላማና ትርጉም ሊኖረው ከቶ አይችልም ። ኢፍትሐዊነትን ዛሬ እንቀበለው ቢባል በመጀመርያ ደረጃ ራሱ ኢፍትሐዊነትን መቀበል ሊኖር የሚገባውን ዘላቂ ሰላም ገና ከጅምሩ መናድን እንደሚያስከትል መታወቅ አለበት ። ሁለተኛ ኢፍትሓዊነትን ዛሬ ያ ሁሉ መስዋዕትነት በተከፈለ ማግስት የምንቀበል ከሆነ ትላንት የተፈጸመብንን ኢፍትሐዊነት ገና ኪሳራ ሳናስከትል ለምን አልተቀበልንም ? ጦርነት ውስጥ ለምን ገባን ? የሚሉ አገባብነት ያላቸው የዜጎች ጥያቄን በተሟላና ሎጂክን በተከተለ መስመር ለመመለስ መቻል አለብን ። ይህንን መመለስ ካልቻልን ከነባራዊ ሀቁ ስለምንርቅ "አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ" እንደሚሆን ከወዲሁ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል ። ይህንን ሀቅ "ወዳጆቻችን" ስለገፋፉን ለመለወጥ አንችልም ። የዛሬ ወዳጆቻችን ነገ ጥቅማቸው ቢነካ ጠላቶቻችን ሊሆኑ እንደሚችሉ ፡ ዛሬ ሊሰጡን ቃለ የገቡልን ነገር ቢኖር ነገ ቃላቸውን ሊያጥፉ እንደሚችሉ ፡ ዛሬ በጫና እነሱ የሚፈልጉትን ነገር ብናደርግላቸው ነገም እየተጫኑ በሉዓላዊነታችን ላይ ሌላ ጫና እንደሚፈጥሩ ፡ ከወዲሁ በመገንዘብ አርቀን መመልከት እንደሚኖርብን መገንዘቡ አገባብነት ይኖረዋል ። እዚህ ላይ "ዘላቂ ጥቅም እንጂ ዘላቂ ፍቅር የለም" የሚለውን ያገሮች እምነት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ከመሪዎቻችን ይጠበቃል ። "ወዳጆቻችን ስለገፋፉን" ዛሬ እነሱን ለማስደሰት ሕጋዊና ፍትሓዊ ባልሆነ መንገድ ሉዓላዊነታችንን አሳልፈን ብንሰጥ ፡ ነገ "የገፋፉን ወዳጆቻችን" ጠላት ቢሆኑብን ወደን የምናስረክበው ሉዓላዊነታችንን መልሰን ለማግኘት ፈጽሞ አንችልም ። በዚህ ፍትሓዊም ሕጋዊም ባልሆነ ፍርደ ገምድል ብይን የሚጎዳው በነዚህ ለኤርትራ በሚከለሉ አከባቢዎች ነዋሪ ህዝባችን ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብና ታሪክ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ። በነዚህ ዛሬ ለኤርትራ እንዲጸኑ ስምምነት እየተደረሰባቸው ባሉ ሉዓላዊ ግዛቶቻችን ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ወገኖቻችን ሞት ፡ ስደት ፡ ረሀብና ቸነፈር ፡ መፈናቀል ብቻ ሳይሆን ባባቶቻችን ደምና አጥንት የተከበረውን ዳር ድንበርና ታሪክን ፡ የዚህ አኩሪ ታሪክ ባለቤት የሆኑት አባቶቻችንና እናቶቻችን ህያው ቅርሶችንም ጭምር ለቀው መሰደድ ሊኖርባቸው ነው ። ቤት ንብረቱን አስጥሎ ቢያስወጡት ይህ ከላይ የተጠቀሰው  ሁሉ ችግርና መከራ እንደሚገጥመው እንኳን የችግሩ ሰለባ የሚሆነው ወገን ቀርቶ እንደባዳ ማንነቱን ሊያስጥሉት ሌት ተቀን የሚሠሩ ወገኖችም ቢሆኑ ይገነዘቡታል ። በዚህ ምክንያትም ያ ህዝብ ችግሩን ከቀያው ወጥቶ ለመመከት ከመሞከር ይልቅ ገና ቤቱን ፡ ታሪኩን ፡ ንብረቱንና ሉዓላዊነቱን ከቀያው ሳይነቀል መከላከል ፡ ማስጠበቅና ማስከበር እንዳለበት በሚገባ ይገነዘባል ። በዚህ ምክንያት የሚከተለው ፡ እንፈልገዋለን የምንለው ሰላም መሆኑ ይቀርና እንከላከለዋለን

የምንለው አውዳሚ ጦርነት ይከተላል ። ስለዚህ የተፈለገው ዘላቂ ሰላም ከሆነ ፡ የሚገኘው ኢ.ሕጋዊና ኢ.ፍትሓዊ የሆነ ውሳኔ በመቀበል ሊሆን እንደማይችል ማንም ንጹሕ ኅሊና ያለው ሰው የሚረዳው ነው ብለን እናምናለን ።

<u>በአራተኛ ደረጃ</u> ፤ በገጽ 4 ላይ ". . . . ማነኛውንም ጉዳይ በትእግስት ፡ በውይይትና ሰጥቶ በመቀበል መርህ በሚካሄድ ድርድር ለመፍታት ያላቸውን ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል ።" የሚል ይገኛል ። በዚህ የሰላም ዕቅድ ላይ የህዝብ ተሳትፎ መነፈግን አስመልክተን ከላይ የገለጽነው እንዳለ ሆኖ በተለይ "ሰጥቶ መቀበል" የሚለው ላይ ስናተኩር የምንሰጠው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ይቸግረናል። ኢ.ትዮጵያ ከኤርትራ የወሰደችው መሬት የለም ። መንግሥታችን ከባድመ ውጭ ስላሉት በፍርደ ገምድልነት ለኤርትራ ስለተወኑ አከባቢዎች ያነሳበት አንድም አጋጣሚ የለም ። ከዓገረለኾማ ጀምሮ እስከ አድጋዲ ዓረ (እንዳልገዳ) ድረስ ወደ ኤርትራ ስለተከለለው ፡ ወደ ኤርትራ ስለተከለሉት የጉለመኻዳ ግዛቶችና ሌሎች በመንግሥታችን በኩል ስማቸው ሲነሳ አለመስማት እንቆቅልሽ ሆኖብናል ። ወደ ኢ.ትዮጵያ የተከለለ የኤርትራ ግዛት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሰጥቶ መቀበል ማለት ምን እንደሆነ ለኛ ሊገባን የሚችል ጉዳይ አይደለም ። የወሰድነው የኤርትራ መሬት በሌለበት ሁኔታ "ሰጥቶ መቀበል" ጭራሽ ትርጉም ያጣል ። በዚህ "ሰጥቶ መቀበል" የሚባል ድርድር ለኢ.ትዮጵያ ትርጉም አይኖረውም ።

<u>በአምስተኛ ደረጃ</u> ፤ በገጽ 5 ላይ "ባጭሩ የሰላም . . . ከኤርትራ መንግሥት ጠንካራ ተቃውሞ የገጠመው መሆኑና ዋናዎቹ የሰላም ኃይሎች ደግሞ . . . . . ጥረታችንን በሙሉ አቅማቸው እንዳይደግፉ የተለያየ እንቅፋት እንዳጋጠማቸው ግልጽ ሆኗል ። . . ቀደም ሲል ያቀረብነው አማራጭ የመፍትሔ ሃሳብ የሚፈለገውን ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ሊያረጋግጥ እንዳልቻለ ግልጽ ሆኗል ።" ይላል ። ከዚህ የምንረዳው መንግሥታችን በመርህ የሚያምንባቸው የዘላቂ ሰላም መርሆዎችን ነድፎ ለመጓዝ መቸገሩን ነው ። በመሆኑም ሻዓቢ.ያ ወደሚፈልገው ግብ ያደርሰኛል ብሎ ያመነበትን መንገድ ይዞ ሲጓዝ በኢ.ትዮጵያ በኩል የተለያዩ የሰላም ሙከራዎች ሲቀርቡ ይስተዋላል ። ይህ ማለት ሻዓቢ.ያ ባለበት ቆሞ ኢ.ትዮጵያ በየጊዜው የተለያዩ መፍትሔዎችን ለመሻት ስትራወጥ ይመለከታል ። እዚህ ላይ ሁለት የተለያዩ እድምታዎች እንዳሉ ለመገንዘብ ይቻላል ።

ይኸውም ፡ መጀመርያ የሚፈለገውን ሰላም ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሻዓቢ.ያ አንድ አቋም ይዞ ሲ.ደርቅ ኢ.ትዮጵያ ለሰላም ፍለጋ የተለያዩ አማራጮችን ለማቅረብ የምታደርገው ጥረት ስንመለከት ዋናው የሰላም ቁልፍ ሻዓቢ.ያ እጅ ውስጥ እንዳለ ሆኖ እንዲ.ታይ እያነሳው እንደሆነ እንገነዘባለን ።

ሁለተኛው ሻዓቢ.ያ ከያዘው ምሽግ ፍንክች ባላለበት ሁኔታ የኢ.ትዮጵያ የሰላም ጥረት በየጊዜው መለዋወጡ ሻዓቢ.ያ አሁንም ፍንክች ሳይል ባለበት ቦታ ቆሞ ሉዓላዊ ገዛቶቻችንን ለመረከብ እንዲቋምጥና ለሰላማዊ ውይይት በር እንዳይከፍት የሚገፋፋው ይሆናል ።

በዚህም በየጊዜው በመለዋወጥ የሚቀርበው የኢ.ትዮጵያ የሰላም ፍላጎት ከኤርትራ መሪዎች ጥረት አንጻር ሲታይ የሚያስተላልፈው መልእክት አሉታዊ እንዲሆን ያደርገዋል ብለን ከልብ ሰግተናል ።

ስለዚህ እነዚህ አንኳር አንኳር ናቸው ብለን ባመንባቸው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሰላም ዕቅዶች ላይ ያሉንን ጥያቄዎች ከላይ ባጭሩ ባስቀመጥነው መልክ ስንዳስሳቸው የምንፈልገው ሰላም እጅጉን እየራቀብን እንደመጣ ተገንዝበናል ።

እዚህ ላይ በበኩላችን የምናቀርበው ወሳኝ ፣ ዘላቂና ሁሉንም ሰላም ወዳድ ኃይሎች ሊቀበሉት ይገባል ብለን የምናምንበት የሰላም ንድፍ አቅርበናል ። ዛሬ በማንም ጀብደኛ የዋሆች ልንባል እንችል ይሆናል ። መጨረሻ ላይ ግን ዞረን ዞረን ሁላችንም ከከሰርን በህዋላ የምንመለስበት ሃቀኛ የመፍትሔ ሃሳብ ነው ብለን እናምናለን ።

ይኸውም በነዚህ አንዳዶች ”አከራካሪ” እያሉ በሚጠሩዋቸው አከባቢዎች የሚኖሩ የሁለቱ አገሮች ህዝቦች ሽማግሌዎቻቸውን ከየራሳቸው በፈቃዳቸው ሰይመው ድንበሮቻቸውን እንዲወስኑ ሁለቱ መንግሥታት እንዲሰማሙ ነው ። ሁለቱ የአከባቢው ነዋሪ ህዝቦች ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ዳር ድንበራቸውን የምያውቁት ኢህዴግም ሆነ ሻዓቢያ ከመፈጠራቸው በፊት መሆኑ መታመን አለበት ። ይህንን ሃቅ ዛሬ ጉልበተኛ ስለሆነ ብቻ ሊለውጠው አይችልም ። ሁለቱ መንግሥታት ያገር ሽማግሌዎቹን ውይይት ፋሲሊተይት ከማድረግ ያለፈ ተራ ሳይኖራቸው የመጨረሻውን የሁለቱ ወገን ሽማግሌዎች ስምምነት ሕጋዊ አርገው በመቀበል በማጽደቅ ላይ ብቻ እንዲወሰኑ ቢሰማሙ የሚፈለገው ዘላቂ ሰላም ሊገኝ እንደሚችል ያለጥርጥር መናገር ይቻላል ።

ከዚህ ውጭ በማነኛውም ዓይነት መንገድ ቢሰላ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ ፈጽሞ እንደማይችል በድፍረት ለመተንበይ እንችላለን ። ከዚህ ውጭ በሆነ ይሁን መልክ ሉዓላዊ የኢሮብ መሬትን ለመቆጣጠር የሚሞክር ወገን ቢኖር ፡ የኢሮብ ህዝብ ኢትዮጵያዊነትን የሚቃጣ ወገን ቢኖር ፡ ውጤቱ ዘላቂ ሰላም ሳይሆን ዘላቂ ደም መፋሰስ እንደሚሆን ማንም ሓላፊነት የሚሰማው ወገን ሁሉ ከወዲሁ እንዲገነዘብልን እንጠይቃለን ። እየጠየቅን ያለነው ከፈተኛ ነገር አይደለም ። ጥያቄያችን የተባበሩት መንግሥታት ሰነዶች የተቀበሉተና ያጸደቁት የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ ነፃነት ወቅት ተግባራዊ ያደረገውና ፡ በአቋም ደረጃም በሕገ መንግሥቱም የተቀበለውና ያጸደቀው የብሔር ብሔረሰቦች መብት እንዲከበርልን ነው ። በጉዳያችን ላይ እኛ ባለቤቶቹ እንደባይተዋር ተቆጥረን ሌሎች አይወስኑልንም ነው ጥያቄአችን ። በጉዳያችን ላይ እኛው እንምከር ነው ጥያቄአችን ። ጥያቄአችን የመብት ጥያቄ መሆኑ ግንዛቤ ይሰጠው ነው ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ህዝብና ምንግሥት ይህንን ጥያቄአችንን ትኩረት ሰጥተው እንዲመለከቱት እያሳሰብን ቀጣይ እርምጃዎችን እንደተለመደው እየተከታተልን እንደምንዘግብ እናስታውቃለን ።

ሉዓላዊነታችን ተከብሮ ለዘላለም ይኖራል ! !

የኢሮብ ኮሚኒቲ በሰሜን አሜሪካ ።
ታኅሣሥ 1997 ዓ.ም ።